# ዶክተር አቢይን በቤት ስራ አጣደፍናቸው

03/29/2018

አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የተመረጡትን ዶክተር አቢይ አህመድ እስካሁን በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች የብዙዎችን የተስፋ ስሜት ያጫረና በተወሰነ ደረጃም ከኢሃዴግ ባህርይ በመነሳት አቢይ ሊፈይዱት የሚችሉት ብዙ ነገር እንደሌለ ሲነገር ይስተዋላል። በበኩሌ በመጀመሪያው የተስፋ ረድፍ ላይ የተሰለፍኩ ሲሆን ለምን እንደሆነም ከመመረጣቸው በፊት በፌስ ቡኬ ላይ ገልጫለሁ። ከኢሃዴግ ባህርይዎች የመጨረሻ አስቀያሚው ህዝብ በትግሉ የሚጎናጸፋቸውን ድሎች ወይም የተለያዩ የህዝብ ጥያቄዎችን በራሱ አነሳሽነት ያደረጋቸውና የድርጅቱ የጥንካሬ አካል አድርጎ በማቅረብ እራሱን የሚያታልልበት ስልቱ ነው።

ከፖለቲካ ጥበብ አንዱ የተቀናቃኝን ህዝባዊ ተቀባይነት አኮስሶ ማሳየት አንዱ ስልት ቢሆንም ህዝብ እያወቀ እየነቃ ሲሄድ ስልቱ መልሶ እራስን የሚዋጋበት መሆኑ አያጠያይቅም ። ኢሃዴግም ዛሬ ራሱን በዚያ ደረጃ ላይ በማድረሱ ምንም በጎ ነገር ቢያደርግ በጥርጣሬ ከመታየት ሊድን የሚችልበት ሁኔታ የለም። ለኔ ከእንግዲህ ህወሃት ህውሃት እያሉ መጮሁ የሚያስኬድ የፖለቲካ ስልት አይደለም። ኢሃዴጎች ካልተባበሩ የህወሃት የበላይነት የሚባል ነገር የለም ። የሰራዊት አመራሩ ደህንነቱ ኢኮኖሚው በህውሃት ተይዞአል አዎ ተይዞአል ግን መሻሻሎች እየታዩ ነው ። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂው ሁሉም የኢሃዴግ ድርጅቶች በፍርሃትም በጥቅምም አብረውት ስለቆሙ ነው። ይህን ፍርሃትና የጥቅም ግንኙነት ሰብረው ሲወጡ የህወሃትን የበላይነት እንዴት እንዳኮሰሙኑት በነለማ በነአቢይ በነገዱ በሌሎችም የማናውቃቸው የድርጂቱ ሰዎች ያለፉት ወራት እንቅስቃሴ ለማየት ተችሎአል። እነለማ ይህን ድፍረት ያገኙት ከየትም አይደለም ከህዝብ ነው። ብሶት የወለደው የህዝብ ቁጣ ውጤት ነው። የህዝብ ቁጣ ደግሞ በአግባቡ ካልተያዘ ጥቅምም ጉዳትንም አስከትሎ ይመጣል ።ለዚህ ነው ህዝብ አዲሶቹን ኢሃዴግ ውስጥ ያሉ የለውጥ አቀንቃኞችን ኢሃዴግም ብትሆኑ ለለውጥ እስከተዘጋጃችሁ እንቀበላችሁዋለን የሚል ድምጹን እያሰማ ያለው ። ለዚህ ደግሞ ሃገር ውስጥ ሆነው በሰላማዊ ትግል እንታገላለን የሚሉት ድርጅቶች ቀርቶ በውጭ በትጥቅ ትግልም ያሰቡት እንኳን ቀናና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመፍትሄ አካል ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን በሰሞኑ መግለጫቸው ያሰሙን።

ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ህዝብና እንታገልለታለን ለምንለው የፍትህ የዲሞክራሲና የ እኩልነት ስራት ፈር ቀዳጅ አካሄድ ነው። ከዶክተር አቢይና መሰሎቹ የሚጠበቀውም ዩህን ወርቃማ እድል መጠቀም ነው። ዶክተር አቢይ በውጭና በሃገር ካሉ በድርጂትም በግለሰብ ደረጃ በርካታ የቤት ስራ ተሰጥቶአቸዋል። ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የተከማቸውን ብሶት ለዶክተሩ ማሸከም ብቻ ሳይሆን በረዥምና በአጭር ጊዜ ሊፈቱ የሚችሉ :በግለሰብ ደረጃና በድርጂት ደረጃ ሊፈቱ የሚችሉትን ችግሮቹን ለመፍታት የህዝብ ሙሉ ተሳትፎ የሚያስፈልጋቸውን : ተቃዋሚው ችግሮቹን በመፍታት ረገድ ሊያበረክት የሚችለውን የበኩሉን ድርሻ : ስር የሰደዱትንና በቀላሉ ሊፈጸሙ የሚችሉትን : ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስፈልገውን ኢኮኖሚያዊ አቅምና ጉልበት፤ የውጭ ሃይሎች አሉታዊና አዎንታዊ ግብአቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባቱ ለዘላቂ መፍትሄ ወሳኝነት አለው። ጠቅለል ሲልም ፋታ ወይም ጊዜ የሚያሻቸውን ለይቶ ማስቀመጥ ማለት ነው። ከሌሎች ወገኖቼ ጋር የምስማማበት 3 መሰርታዊ ከወር በላይ የማይፈጁ ለምሳሌ

1/ እስረኞችን መፍታት

2/ የአስቸኩዋይ ጊዜያዊ አዋጁን ማንሳት

3/ ብሄራዊ የሰላም ኮንፍረንስና ተቃዋሚዎችን ለውይይት መጥሪያ ጊዜውን መወሰን ዋናዋናዎቹ ናቸው።

ከ እንግዲህ የሃገሪቱን ችግር ለመፍታት ኢሃዴግ ብቻውን የሚወስነው ጉዳይ ሳይሆን ስለሃገሬ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ከነመፍትሄ ሃሳባቸው እንዲቀርቡ የተወሰነ ጊዜ ሊኖር ይገባል ። ለዚህም ይህን ጉባኤ ለማዘጋጀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ አዘጋጅ ግብረ ሃይል በአስቸኳዋይ ማቋዋቁዋም አስፈላጊ ይሆናል ። ከ 100 በላይ የፖለቲካ ድርጂት ባለበት ሃገር 100 የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ የውዝግብ መድረክ እንዳይሆንም በተጨመቁ የመፍትሄ ሃሳቦችን እንዲኖር ለተቃዋሚዎች የአጀንዳ ማቅረቢያ ጊዜና እድል እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

እንግዲህ የዶክተር አቢይ ሚና ይህን የፖለቲካ ጨዋታ በአግባቡ በተሰጣቸው ስልጣን መጫወት ነው ። ውስብስብ ችግር ያለበትን የሃገር መሪነት ቀርቶ ቤተሰብን መምራት ት እግስትና ድፍረትን ይጠይቃል ። መሪነት ቦታ ላይ ተቀምጦ ነገሮችን ማየትና በሃሳብ ሃገርን መምራት ይለያያሉ ። እስካሁን ባለመታደልም ሆነ ከስልጣን በሃይል አጨባበጥ ባህሪይ የተነሳ መሪዎቻችንን እንደህዝብ ያገዝንበት ጊዜ የለም ። ደካማ ጎናቸው እንጂ ግለሰባዊ ጥንካሬያቸውን ተጠቅመን

እንደ ህዝብ ያበረታታንበት ወቅት የለም ። ስልጣን ላይ ወጥተው እንጂ ሳይወጡ አልገመገምናቸውም ። ምናልባት ዶክተር አቢይ ይህን ቅድመ ግምገማ እድል ካገኙት ግለሰብ መሪ የመጀመሪያ ናቸው ማለት ይቻላል።

ኢሃዴግ እኔ መረጥኩዋቸው ይበል እንጂ ምርጫው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ህዝባዊ ተሳትፎ አለው። ማንም ሆነ ማን ኢሃዴግ እስካለ ለውጥ አይመጣም ብለን የምናስብ ሰዎች ኢሃዴግን የለውጡ አካል ብናደርገው የሚል በጎ አስተሳሰብ ወደ አእምሮአችን ለማስገባትም እናስብ። ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውም ። ከመገዳደል ከመጠፋፋት ፖለቲካ ከዘለልን በርግጥም ለዲሞክራሲ ዝግጁነታችንን የሚያረጋግጥ ነው። ዶክተር አቢይ ሲናገሩ እንደሰማሁት ለተከታዩ ትውልድ ወደፊቱን እናሳምርለት ያለፈው ታሪክ ለወደፊታችን የማይበጀን ከሆነ አደጋ አለው ነው ያሉት ። እንድንወዳቸው ያደርገንም ይሄው ነው። የመደመር እንጅ የመቀነስ ፖለቲካን የማይፈልጉ መሆናቸውን ነው። ሰውን በመግደልና በማሰር ለውጥ እንደማይገኝ ሲናገሩም አድምጠናል ። ይህ የሰለጠነ አስተሳሰባቸው ነው ቀልባችንን የሳበው። ስልጣን ከያዙ በሁዋላ ሰው እንደማይገደል እርግጠኛ ባንሆንም ለተገደለ ሰው ፍትህ ማግኘት ማስቻላቸውን ነው ። ሰው ሃሳቡ ሊታፈን አይገባም ሊጽፍ ሊናገር ሃሰቡን በተቃውሞ ሊገልጽ ይገባዋል ብለውናል ። ስለ ህዝቦች ፍቅርና አንድነት የሚጽፍ እንዳለሁሉ ህዝብን የሚያጋጭ ህዝብን የሚከፋፍል ጸሃፊ እንደሚኖር ይታወቃል ባለፉት ዘመናት እነተስፋየ ገብረአብን የሚያበረታታ እነ እስክንድርና ተመስገንን የሚያሰቃይ ዘመን ተገልብጦ እንድናይ ነው የምንፈልገው። ዶክተር አቢይ ጥሩ ወደ ዲሞክራሲያዊ ስራት የሽግግር መሪ እንዲሆኑ የምንመኝ ሁሉ የአቢይን የግል ሰብእና ከሃገር እንጅ ከድርጅት ጋር ብቻ ባናቆራኘው መልካም ይሆናል። ድርጅት የሰዎች ስብስብ ነው። በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥም ሆነ ማህበራዊ ስብስብ ውስጥ ደግሞ ቀና በጎ አስተሳሰብ ያላቸው እንዳሉ ሁሉ ዘወትር ስቃይና መከራን እንደፖለቲካ መስመር የሚያራምዱ ይኖራሉ ። ይህን ጠንቅቆ ማወቅና ወደበጎ አስተሳሰብ ማምጣት የሁሉም ዜጋ ድርሻ ነው። የማይታለፈው ግን ፖለቲካ ነውና በተሻለና ወቅቱን የመጠነ የፖለቲካ አካሄድ ህዝብ ለነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል ቀጣይነት ማጠናከር ነው። ነጻነት ምን ጊዜም ይደፈራል። ነጻነት አንጻራዊ ነው። ህብረተሰብ በመደብ በጥቅም እስከተከፋፈለ ድረስ አንዱ የአንዱን ነጻነት ለመግፈፍ መሞከሩ አይቀርም ። ነጻ ነኝ የሚለው ሃገር የሌላውን ሃገር ነጻነት ለመግፈፍ ምን ያህል እንደሚሞክር በአለም ላይ ያሉ ጦርነቶችን ማየት ተገቢ ነው። ለነጻነት የሚደረግ ትግል አይቆምም። ዶክተር አቢይም ለሃገሩ ብቻ ሳይሆን ለራሱም የአስተሳሰብ ነጻነት መታገሉ የማይቀር ነው። ስለሃገሩ ነጻነት የሚያስብ ደግሞ አስቀድሞ ከማንኛውም የቡድን አስተሳሰብ የበለጠ የራሱ አስተሳሰብ ባለቤት ሊሆን ይገባዋል ። ያኔ የተሙዋላ ሰብ እና ይኖረዋል። ዶክተሩን እንደሰማሁዋቸው ያን የሚያሙዋሉ ይመስላል። የመጀመሪያ ንግግራቸው ይህን ዩበልጥ ቢያረጋግጥ ደስ ይለኛል።

ጊሼ ጊሻ